አንፃር የተለየ ክብካቤ የሚፈልግ ከመሆኑ ጋር ተሰናስሎ የሚያስፈልጋቸው ማህበራዊ መድህን ነው። ሌላው የጤናቸውን ሁኔታ የሚጨምረውና እንደ ትራንስፖርት፣ መጠለያ ቤትና ሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን ማግኘት የሚያስችላቸው፤ አምስተኛው ደግሞ በብዙ ተጋላጭ የሆኑበትን ጥቃትና በደልን መከላከል ነው።

በየትኛውም ሁኔታና ቦታ ለአረጋውያን ክብር መስጠት ያስፈልጋል ይህውም በትራንስፖርት ውስጥ አገልግሎት ሲፈልጉ እንዲሁም በየትኛውም ቦታ ለአገልግሎት ሲመጡ ቅድሚያ በማስቀደም እድሉን እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የአረጋውያን ውለታ በቀላሉ ተከፍሎ የማያልቅ ቢሆንም ቢያንስ እንኳን ውለታቸውን ለመጭው ትውልድ ለማስገንዘብ ይቻል ዘንድ በዓለም አቀፍ እና በአገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ መሪ ቃሎች የአረጋዊያን በዓል ቀን ሲከበር ቆይቷል፡፡ ዘንድሮም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ32ኛ ጊዜ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ ለ31ኛ “የአረጋዊያን የኢትዮጵያዊነት አሻራ ለትውልድ አደራ” በሚል መሪ ቃል እየተከበረ ይገኛል፡፡



**በአዲስ አበባ ኮሙኒኬሽን ቢሮ**

**የሚዲያ ይዘት ማበልፀግና ሥርጭት ዳይሬክቶሬት**

**የህትመት ውጤቶች ዝግጅትና ስርጭት ስራዎች ቡድን የተዘጋጀ**

*Websites* http://www.cityaddisababa.gov.et/

የአዲስ አበባ ከተማ ኮሙኒኬሽን ቢሮ
Addis Ababa City Communication

addisababacommunication@gmail.com

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሙኒኬሽን ቢሮ
Addis Ababa City Administration Communication Bureau

# "አረጋውያን የማህበረሰቡ ውድ ሃብት ናቸው"




ህዳር 2015 ዓ.ም

አረጋውያን የዕድሜ ባለጸጋና ናቸው፡፡ በዚህ ዕድሜያቸው ውስጥ የታመቁ ዕውቀቶች፣ ልምዶች እና ጥበቦች ይገኛሉ፡፡ ዕድሜ ከቀለም ብቻ ሳይሆን በተግባር እና በኑሮ በርካታ ጠቃሚ ትምህርቶችን አስተምሯቸዋል፡፡ አረጋዊያን በወረቀት ላይ ሳይሆን በልቦናቸው የተጻፉ የበርካታ ጠቃሚ ታሪኮች ባለቤትም ጭምር ናቸው፡፡ ባጠቃላይ አረጋዊያን ሀገር ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ስለዚህ ሀገር ማለት ሰው ነው ብለን ከተግባባን አረጋዊያን በእርግጥም ሀገር ናቸው፡፡

እንግዲህ ጠጋ ብሎ በታላቅ አክብሮት ላዳመጣቸው ተዝቆ የማያልቅ የዕውቀት፤ የጥበብ እና የልምድ ምንጭ መሆናቸውን መረዳት አያስቸግርም፡፡ አንድ በጣም ታዋቂ የሆነ የዩኒቨርሲቲ መምህር እና ተመራማሪ በአንድ ወቅት የምድራችን ትልቁ ሀብት የት እንደሚገኝ ታውቃላችሁ ብሎ ተማሪዎቹን ጠይቆ ነበር፡፡ እኘም ተማሪዎቹ ብዙ ሞክረው መመለስ ቢያቅታቸው በመቃብር ነው ብሎ መልሶላቸው ነበር፡፡ ምክንያቱም ብዙ አረጋዊያን በዕድሜ ዘመናቸው ያካበቱትን ልምድና የቀሰሙትን ትምህርት ይዘው ስለሚሞቱ ነው፡፡ ይህ አስገራሚና የሚቆጭ እውነት ዛሬም በግልጽ የሚስተዋል ጉዳይ ነው፡፡ አረጋዊያን ያካበቱትን ትልቅ የአእምሮ ሀብት ጠጋ ብለን እንደዋና ሃብት ሳንወርሰው ቢሞቱ ምን ያህል ይቆጫል? እነሱም እኮ መደመጥ ይፈልጋሉ፡፡ አደራ ሊሰጡን የሚፈልጉት በርካታ ሀገራዊ ጉዳዮች አሏቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አረጋውያን ራሳቸው ክብራችን ናቸው፡፡ እነሱ ያልተገኙበት የትኛውም ባህላዊ፣ መንግስታዊ እና ህዝባዊ ሁነት ክብር ይጎድለዋል፡፡ በአንጻሩ ግን እነሱ የታደሙበት እና የመረቁት ሁነት ምን ያህል ስኬታማ፣ ድባቡም ክብር ያለው እንደሆነ በተግባር ማየት እና ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

አረጋውያን ያልተገኙበት በዓልና ሽንጎ ሞገስ እንደሚጎለው ሁሉ እነርሱ ያልተገኙበትና ያልመረቁት የትኛውም ሀገራዊ አጀንዳ ለውጤት ሊበቃ አይችልም፡፡ ምክርና መላ ከአረጋዊያን አይጠፋም፡፡ ተናግረው የሚያሳምኑበት ርዕቱ አንደበት አላቸው፡፡

አረጋውያን የዚህች ሀገር ትልቅ ባለውለታ መሆናቸው ሌላው እንድንከባከባቸውና እንድናከብራቸው የሚያደርገን በቂና አሳማኝ ምክንያት ነው፡፡ ማን ያውራ የነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ እንዲሉ በአፍሪካ ብሎም በዓለማችን አደባባዮች ታፍራና ተከብራ የኖረች ሀገር ለማቆየት ያልወጡት ዳገት፣ ያለወረዱት ቁልቁለት እንደሌለ ታሪካቸው በወረቃማ ብዕር ተጽፎላቸዋል፡፡ እኛ በነጻነትና በክብር እንድንኖር ከህይወት፣ ከደምና ከአጥንት ትልቅና ውድ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ስለሆነም አረጋዊያን ከማንም በላይ እጥፍ ድርብ ክብር ሊሰጣቸውና ክብካቤ ሊደረግላቸው የሚገባቸው ናቸው፡፡አረጋውያን ወገን እያላቸው እንደሌላቸው ተርበው፣ ታርዘው እና ለጎናቸው ማረፊያ አጥተው ሲንገላቱ ማየት ያማል፡፡

አረጋዊያን በራሳቸው ወገን በአደባባይ ሲዋረዱ ማየት ልክ ሀገር እንደተዋረደች ያህል ሊያንገበግበን ይገባል፡፡

የአረጋውያንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ብሄራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ ላይ የተቀመጡ አምስት የትኩረት መስኮች ሲኖሩ ሁሉም አረጋዊያንንም ይመለከታሉ። እነሱም የሴፍትኔት መርሐ ግብር፣ የሥራ ስምሪትና የተሻሻለ የኑሮ ሁኔታ መፍጠር ሲሆኑ የጤንነት ሁኔታቸው ካሉበት የዕድሜ ደረጃ

